## የጊዜው ፡ አሳሳቢ ፡ ጉዳይ ፤

## በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በመንግሥትና ፡ በግል ፡ ባ[illegible]ቶች ፡ መካከል ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኝ ፡ ድንጋይ ፡ የሚደረ[illegible] ክርክሮች

ሃሪሰን ፡ ሲ ፡ ዳኒንግ ።*

ኢትዮጵያ ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ሕገ ፡ መንግሥቷን ፡ ባሻሻለች ፡ ጊዜ ፡ ካዳዲሶቹ፡ አንቀጾች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ "የተፈጥሮ ፡ ሀብትን ፡" የሚመለከት ፡ ነበር ። በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከት ፡ አንቀጽ ፡ አልነበረም ። ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ የወጡ ፡ አንዳንድ ፡ ሕጐችም ፡ ቢሆኑ ፡ የተበታተኑና ፡ ያልተቀነባበሩ ፡ ስለነበሩ ፡ አዲስ ፡ መንገድ ፡ ለመክፈት ፡ ሁኔታው ፡ ያመቹ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ ሁኔታ ፡ በመጨረሻ ፡ የተገኘው ፡ የተሻሻለው ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴[1] ፡ የጥሩ ፡ አጻጻፍ ፡ አርአያ ፡ ባይሆንም ፡ ስለ ፡ አንዳንድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ፡ የንብረት ፡ ክፍሎች ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ መሆንና ፡ በመንግሥት ፡ በኩል ፡ ስላለው ፡ ቁጥጥር ፡ የሚመሠርቱ ፡ ጠቃሚ ፡ መምሪያዎችን ፡ ይሰጣል ። ከመምሪያዎቹም ፡ አንዱ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ "የተከበሩ ፡ ቅርሶችና ፡ የሕዝብ ፡ ገንዘቦች ፡" በመሆናቸውና ፡ "ለአሁኑም ፡ ለሚከተለውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ትውልድ ፡" ጥቅም ፡ እንዲውሉ ፡ "በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ሕግ ፡"[2] እንዲጠበቁ ፡ የሚል ፡ ነው ። ሌላም ፡ መምሪያ ፡ አንዳንድ ፡ የንብረት ፡ ዓይነቶችን ፡ "የመንግሥት ፡ ንብረት፡" ያደርጋቸዋል ።

---

* በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ረዳት ፡ ፕሮፌሰርና ፡ ረዳት ፡ ዲን ።

1. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡-
   ሀ/ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ በመሬቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ ከውኃ ፡ በታች ፡ ያለውም ፡ ጭምር ፡ የመንግሥቱ ፡ ንብረት ፡ ነው ።
   ለ/ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ በውኃዎቹ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶችና ፡ ደኖቹ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ መሬቱ ፡ አየሩ ፡ ሐይቆቹ ፡ ወንዞቹ ፡ ጠረፎቹ ፡ ሁሉ ፡ ለአሁኑም ፡ ለሚከተለውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ትውልድ ፡ ጠቃሚዎች ፡ እንዲሆኑ ፡ የተከበሩ ፡ ቅርሶችና ፡ የሕዝብ ፡ ገንዘቦች ፡ ናቸው ። የእነዚህ ፡ ሀብቶች ፡ መልካም ፡ አጠባበቅ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ልማት ፡ እጅግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ለነዚህ ፡ ሀብቶች ፡ መልካም ፡ አጠባበቅ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የሚስማሙትን ፡ አስፈላጊና ፡ ተገቢ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ያደርጋል ።
   ሐ/ ስለነዚህ ፡ ሀብቶች ፡ አጠባበቅ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ሕግ ፡ የተወሰነውን ፡ በመተላለፍ ፡ ማንኛዎቹም ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ማንኛዎቹም ፡ ማኅበሮች ፡ በተባሉት ፡ ሀብቶች ፡ ሊጠቀሙባቸው ፡ ወይም ፡ ሊሠሩባቸው ፡ አይችሉም ።
   መ/ በተፈጥሮ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በሆነ ፡ በማንኛውም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ባለው ፡ በማናቸውም ፡ ማኅበር ፡ ስም ፡ ያልተያዘ ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ ባለቤት ፡ ባለመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ የተገኘ ፡ መሬት ፡ የተለቀቁ ፡ ርስቶችና ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ የአፈር ፡ የጫካ ፡ የግጦሽ ፡ መሬት ፡ የባሕሮችና ፡ የወንዞች ፡ ሀብቶች ፡ ሁሉ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረቶች ፡ ናቸው ።
2. ይህ ፡ አነጋገር ፡ ትርጉም ፡ ያለው ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ የኢትዮጵያ ፡ አዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ኤሪትራ ፡ ነፃ ፡ ሆና ፡ በኢትዮጵ ፡ ዘውድ ፡ ሥር ፡ በፌደራስዮን ፡ የምትተዳደር ፡ ሃገር ፡ ስለነበረች ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ለማወቅ ፡ ክፍል ፡ ኤ ፡ አንደኛ ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፺ (፭) ፡ ሬዘሉስዮን ፡ (ውሳኔ) ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ አምስተኛ ፡ ዓመት ፡ ስለ ፡ ኤሪትሪያ ፡ ጉዳይ ፡ ዲሴምበር፡ ፪ ፡ ፲፱፻፶ ፡ (እ. ኤ. አ.) ፡ የሰጠውን ፡ ይመለከቷል ። ይህም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡

የአንቀጽ ፡ ፩፻፴ን ፡ ተገቢ ፡ ትርጉሙን ፡ ለማወቅ ፡ ብንሞክር ፡ ረዘም ፡ ባለ ፡ በሌላ፡ ጽሑፍ ፡ የተጠቀሱት ፡ ብዙ ፡ ችግሮች ፡ ይገጥሙናል ።[3] የዚህ ፡ "የጊዜው ፡ አሳሳቢ፡ ጉዳይ ፡" ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ እነዚህን ፡ ችግሮችን ፡ ለማጥናት ፡ አይደለም ። የጽሑፉ ፡ ዓላማ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በብዛት ፡ የሚነሱትን ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ስላሉት ፡ ድንጋይ ፡ ንብረትነት ፡ ክርክሮች ፡ ላይ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴(ሀ) ፡ ያለውን ፡ አግባብነት ፡ ለማጥናት ፡ ነው ።[4] ይህም ፡ ድንጋይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የምጣኔ ፡ ሀብት ፡ ዋጋ ፡ ስላለውና ፡ ለግልም ፡ ሆነ ፡ ለመንግሥት ፡ የልማት ፡ እቅዶች ፡ ተፈላጊ ፡ ስለሆነ ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ ስላለው ፡ ሁኔታ ፡ ለክርክሮቹ ፡ ተገቢ፡ መፍትሄ ፡ መስጠት ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

<u>በባለንብረቱና ፡ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ድንጋይ ፡ የሚነሱ ፡ ጉዳዮች ።</u>

አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ስላለ ፡ ድንጋይ ፡ የሚነሱት ፡ ነገሮች ፡ ለአውራ ፡ ጐዳናዎቹ ፡ ሥራና ፡ ጥበቃ ፡ ድንጋይን ፡ በብዛት ፡ በሚፈልገው ፡ በአውራ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ ለሚወሰድበት ፡ ድንጋይ ፡ ግምት ፡ ይከፈለኝ ፡ በሚለው ፡ ድንጋዩ ፡ ከተወሰደበት ፡ መሬት ፡ ባለ ፡ ንብረት ፡ መካከል ፡ ነው ። ያልደቀቀ ፡ ድንጋይ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ አካባቢ ፡ ባለው ፡ ገበያ ፡ መሠረት ፡ አራት ፡ ብር ፡ በሜትር ፡ ኩብ ፡[5] ስለሚያወጣ ፡ የሚያከራክረው ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡

---

ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሰፕቴምበር ፡ ፲፭ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ. ኤ. አ.) ያጸደቁት ፡ "ፌደራል ፡ አክት ፡" አንድ ፡ ክፍል ፡ ነው ። የጸደቀበት ፡ አቋም ፡ በኤን ፡ ማሬን ፡ ዘ ፡ <u>ኢትዮፒያን ፡ ኤምፓየር ፡ ፌደሬሽን ፡ ኤንድ ፡ ሎውስ</u> ፡ (፲፱፻፷፭) ፡ ገጽ ፡ ፵፫ ፡ ላይ ፡ ወጥቷል ። ኤርትራ ፡ በፌደረሽን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ መቀላቀሏ ፡ የጸናበት ፡ ሰፕቴምበር ፡ ፲፭ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ (እ. ኤ. አ.) ፡ የተሰጠ ፡ አዋጅ ፡ ቁ ፡ ፩፻፴፬ ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ፲፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁ ፡ ፩ ፡ በተጨማሪ ፡ ይመለከቷል ። ቁ ፡ ፳ ፡ (፪) (ኤች) ፡ የኤርትራ ፡ የ፲፱፻፶፪ ፡ (እ. ኤ. አ.) ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በጄ ፡ ፓል ፡ እና ፡ ሲ ፡ ክላፐሃም ፡ <u>ኢትዮፒያን ፡ ኮንስቲቱሽናል ፡ ዲቨሎፕመንት</u> ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፷፯) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፸፮ ፡ ላይ ፡ እንደወጣው ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ ልማት ፡ በኤርትራ ፡ ስልጣን ፡ ስር ፡ እንዲሆን ፡ አድርጎ ፡ ነበር ። የኤርትራ ፡ ግዛት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ስለመጨመርና ፡ ስለመቀላቀሉ ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ (እ. ኤ. አ.) ቁ. ፯ ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ፲፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁ. ፩ ፡ ስምንተኛ ፡ ክፍል ፡ የ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በዚሁም ፡ መሠረት የተሠሩ ፡ የፌደራሉ ፡ ሕጎች ፡ እንዲሁም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ሕጐች ፡ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ በዚሁ ፡ ትእዛዝ ፡ በኤርትራም ፡ ጭምር ፡ ሆነው ፡ በመላው ፡ በፌደራሉ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ እኤዲሆኑ ፡ ተደርጓል ። ስለዚህ ፡ የአዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ ፡ የ፲፱፻፵፫ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትን ፡ እንደማደሱ ፡ መጠን ፡ የኤርትራን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳(፪) (ሸ) ፡ ተፈጻሚነት ፡ የነሳው ፡ ይመስላል ። ይህን ፡ ማለት ፡ የሚቻለው ፡ ግን ፡ የመቀላቀሉ ፡ ትእዛዝ ፡ ክፍል ፡ ስምንት ፡ በ"ፌደራል ፡ አክት ፡" ስር ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አልተጻረረም ፡ የተባለ ፡ እንደሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

3. አር ፡ በርማን ፡ "በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ ፡ መሠረት ፡ መንግሥት ፡ በተፈጥሮ፡ ሀብቶች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ባለሀብትነትና ፡ ቁጥጥር ፡" <u>የኢት ፡ ሕግ ፡ መጽሔት</u> ፡ ፫ኛ ፡ ቮል ፡ (፲፱፻፶፱) ፡ ገጽ ፡ ፭፻፷፭ ።
4. "ከመሬት ፡ ውስጥ ፡" የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ የምንጠቀምበት ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ድንጋይ ፡ ከመሬት ፡ ወጥቶ ፡ ከሚገኘው ፡ ድንጋይ ፡ ለመለየት ፡ ነው ። ባንዳንድ ፡ ቦታዎች ፡ ይህ ፡ "ከመሬት ፡ ውስጥ ፡" የሚገኘው ፡ ድንጋይ ፡ እስኪታይ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ም ፡ "በመሬት ፡ ውስጥ ፡" የሚሉትን ፡ ቃላት ፡ ሲጠቀም ፡ ይህንኑ ፡ ማለቱ ፡ ይመስላል ።
5. በግምት ፡ ገዢው ፡ መክፈል ፡ ያለበት ፡ ይህ ፡ ነው ። ለሌሎቹ ፡ ጉዳዮች ፡ ድንጋይ ፡ በተለየ ፡ ዋጋ ፡ ይገመት ፡ ይሆናል ። <u>ጣፋ ፡ ሰኝ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መልስ ፡ ሰጭ</u> ፡ (ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፷) ፡ <u>የኢት ፡ ሕግ ፡ መጽሔት</u> ፡ ፳ኛ ፡ ቮል ፡ ገጽ ፡ ፪፻፷፮ ። ንብረት ፡ ለማስለቀቅ ፡ ጉዳይ ፡ አንድ ፡ የሥራ ፡ ሚኒስቴር ፡ መሃንዲስ ፡ የድንጋይ ፡ ዋጋ ፡ በሜትር ፡ ኩብ ፡ ፰ ፡ ሣንቲም ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ገምቷል ።

ሊሆን ፡ ይችላል ። ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ያለ ፡ ድንጋይ ፡ ከግል ፡ መሬቶች ፡ በሚወሰድበት ፡ ጊዜ ፡ ግምት ፡ ይከፈል ፡ የነበረው ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ በነበሩት ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ስላደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ብቻ ፡ ነበር ፤ ለምሳሌ ፡ ድንጋዩ ፡ በወጣበት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ አቅራቢያ ፡ የነበሩትን ፡ ቤቶችን ፡ ወይም ፡ ቡቃያዎችን ፡ ባጠፋ ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፡ ግምት ፡ የሚከፍለው ። ለዚህም ፡ አስተያየት ፡ የሕግ ፡ ድጋፍ ፡ የሆነው ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ንብረት ፡ የማስለቀቅ ፡ መብት ፡ ሰጥቶ ፡ በተወሰደው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ "ቤቶች ፤ አዝመራዎች ፤ አታክልቶችና ፡ ሌሎችም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡" ብቻ ፡ ግምት ፡ እንዲከፍል ፡ የሚያስገድድ ፡ ሕግ ፡ የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንን ፡ ያቋቋመው ፡ አዋጅ ፡ ክፍል ፡ ፰ (መ) ፡ ነው ።[6]

በአንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ ውስጥ ፡ ንብረትን ፡ በማስለቀቅ ፡ ለተወሰደ ፡ "ንብረት ፡ " ሁሉ ፡ "በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ የተቆረጠ ፡ ትክክለኛ ፡ ግምት ፡" እንዲከፈል ፡ የሚለው ፡ የተሻሻለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከታወጀም ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡[7] ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጸው ፡ የክፍል ፡ ፰(መ)ን ፡ ተፈጻሚነት ፡ በጠቅላላ ፡ ተቀብለውት ፡ የነበሩ ፡ ይመስላል ። ጉዳዩ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ያለው ፡ ድንጋይ ፡ የባለመሬቱ ፡ ቢሆንም ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለ ሥልጣንን ፡ ያቋቋመው ፡ አዋጅ ፡ የተወሰኑ ፡ ትርጉም ፡ ያላቸውን ፡ ቃላት ፡ በመያዙ ፡ ለተወሰደው ፡ ድንጋይ ፡ ግምት ፡ እንዳይሰጥ ፡ ያግዳል ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ የነበራቸው ፡ ይመስላል ።[8] የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡[9] ግን ፡ እነዚህን ፡ ጠባብ ፡ አነባበብ ፡ ያላቸውን ፡ ቃላት ፡ ስለሚሽር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በሚገኘው ፡ አስተሳሰብ ፡ ለመገልገል ፡ አይፈቅድም ። አሁን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ንብረትን ፡ በማስለቀቅ ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤትም ፡ ጭምር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሚያዙትን ፡ እንዲከተሉ ፡ ይገደዳሉ ። እነዚህም ፡ ለተወሰዱት ፡ የግል ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ ግምት ፡ እንዲከፈል ፡ የሚያዙ ፡ ስለሆኑ ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ያለው ፡ ድንጋይ ፡ የማን ፡ ንብረት ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ በሙሉ ፡ መመለስ ፡ ያስፈልጋል ። ይህንን ፡ ጥያቄ ፡ በምንመለከትበት ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴፩(ሀ) ፡ ነው ።

---

6. ክፍል ፡ ፰ (መ) ፡ የኢትዮጵ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ (እ. ኤ. አ.) ፡ አዋጅ ፡ ቁ. ፩፻፲፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁ. ፰ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ "ፍክስቸርስ ፡" መጀመሪያ ፡ በአማርኛው ፡ "ሌሎችም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረቶች ፡" በሚል ፡ ተተርጉሞ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ለአማርኛ ፡ ብቻ ፡ በወጣው ፡ ማረምያ ፡ ይህ ፡ ተለውጦ ፡ "ሌሎችም ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ የተሰሩ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡" ተብሎ ፡ እንዲነበብ ፡ ተደርጓል ፡ ማረምያ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ (እ. ኤ. አ.) ፡ ቁ. ፴፰ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፬ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁ. ፩ ።
7. ከዚህ ፡ የተለየው ፡ በቅርቡ ፡ አንድ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንን ፡ ያቋቋመው ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፰(መ) ፡ ለድንጋይ ፡ ግምት ፡ እንዳይከፈል ፡ እያደርግም ፡ በማለት ፡ የወሰነው ፡ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰው ፡ የአቶ ፡ ጣፋ ፡ ሰኝ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።
8. ስለ ፡ አንቀጽ ፡ ፰(መ) ፡ በጠቅላላው ፡ ኤች ፡ ዳኒንግ ፡ "የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቅሙትን ፡ ሀብቶች ፡ የሚያስለቅቅበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡" የኢት ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፩ኛ ፡ ቮል ፡ )(፲፱፻፷) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፺ ፡ ይመለከቷል ።
9. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫ሺ፫፻፵፯ ። በተጨማሪም ፡ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፰ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የኤች ፡ ዳኒንግን ፡ ጽሑፍ ፡ ይመለከቷል ።

### የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፵ ፡ (ሀ) ፤

አንቀጽ ፡ ፩፻፵(ሀ)ን ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ ለመተርጐም ፡ ቢፈለግ ፡ መጀመር ፡ ያለብን ፡ የአንቀጹን ፡ ቃላት ፡ በጥንቃቄ ፡ በመመርመር ፡ ነው ፡- "በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ በመሬቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ ከወኃ ፡ በታችም ፡ ያለ ውም ፡ ጭምር ፡ የመንግሥቱ ፡ ንብረት ፡ ነው ።" ቃላቱን ፡ ብቻ ፡ በመመልከት ፡ ሁለት ፡ አነባበብ ፡ ለመስጠት ፡ ይቻላል ፤ የመጀመሪያው ፡ "(በ)ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡" የሚገኙት ፡ ሀብቶች ፡ "በመሬት ፡ ውስጥ ፡" ያሉትም ፡ ጭምር ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ናቸው ፤ የሚል ፡ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ፡ ከመሬት ፡ ውስጥና ፡ "በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሀብት ፡" ብቻ ፡ ናቸው ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ የሆኑት፡የሚል ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ሁለቱም ፡ አነባበቦች ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ድንጋይ ፡ እንደ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ አድርገው ፡ ሊቆጥሩት ፡ ቢችሉም ፡ የአንቀጽ ፡ ፩፻፵(ሀ) ን ፡ ስፋትና ፡ ዓላማን ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ ከሁለቱ ፡ አነባበቦች ፡ አንዱን ፡ መምረጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። በብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሳ ፡ ሁለተኛው ፡ አነባበብ ፡ ትክክለኛ ፡ ይመስላል ።[10] በመጀመሪያ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ናቸው ፡ ከተባለ ፡ ያገሩ ፡ መሬት ፡ በሙሉ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሌሎች ፡ አንቀጾች ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ የሆኑ ፡ መሬቶች፡ መኖራቸውን ፡ ያወቁ ፡ መሆናቸው ፡ ግልጽ ፡ ነው ።[11] አንቀጽ ፡ ፻፵(ሀ)ም ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ ሀብቶች ፡[12] እንጂ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶችን ፡ ሁሉ ፡ በድንገት፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ለማድረግ ፡ የታሰበ ፡ እቅድ ፡ አይመስልም ። ሁለተኛም ፡ ለተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፵(ሀ) ፡ የነበረ ፡ የዝግጅት ፡ ጽሑፍ ፡ ጥቂት ፡ ቢሆንም ፡ የሚያሳየው ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፵(ሀ) ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሀብት ፡ ብቻ ፡ እንዲመለከት ፡ የታሰበ ፡ መሆኑን ፡ ነው ።[13] በመጨረሻም ፡ "በመሬት ፡ ውስጥ ፡

---

10. በመጀመሪያው ፡ አነባበብ ፡ የመጣው ፡ በእንግሊዘኛው ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፵ (ሀ) ፡ ውስጥ ፡ በቸልተኝነት ፡ በተጨመረው ፡ በመጀመሪያው ፡ ነጠላ ፡ ሰረዝ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

11. ለምሳሌ ፡ ያሀል ፡ የሚከተሉትን ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጾች ፡ ይመለከቷል ፡- ፲፱ (መ) ፡ ፴፮(መ) ፡ ፺፬ ፡ እና ፡ የአንቀጽ ፡ ፩፻፵ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ ፡ (መ) ።

12. የዚህ ፡ ልማድ ፡ መግለጫ ፡ በእዜርቮስ ፡ ላምፒር ፡ ዲትዮፒ ፡ (፲፱፻፴፮ ፡ እ. ኤ. አ.) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷ ፡ ኤፕሪል ፡ ፳ ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ (እ. ኤ. አ.)፡ ቁ. ፩ ፡ "ዴክሬ ፡ ሬግለማንታ ፡ ሌክስፕሎዋታስዮ ፡ ደ ፡ ሚን ፡ ዳን ፡ ላምፒር ፡ ዲትዮፒ ፡" ላይ ፡ ወጥቷል ። በዚሁ ፡ መሠረት የኢትዮጵያ ፡ የመሬት ፡ ውስጥ ፡ ሀብቶች፡ ብሔራዊ ፡ ንብረቶች ፡ ስለሆኑ ፡ ከባለመሬቱ ፡ የባለቤትነት ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ናቸው ። በዜርቮስ ፡ ገጽ፡ ፫፻፲፫ ፡ ቁ. ፯ ፡ ላይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት፡ ስለ ፡ መዓድን ፡ ፍለጋና ፡ ማውጣት ፡ የተሰጠ ፡ ደንብ ፡ ይመለከቷል ። በተጨማሪ ፡ የወርቅና ፡ የፕላቲንየም ፡ ገበያ ፡ ስለመቆጣጠር ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፬ ፡ (እ. ኤ. አ.) ፡ አዋጅ ፡ ቁ. ፷፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፫ኛ ፡ ዓመት ቁ. ፲፩ ፡ መግቢያውን፡ ይመለከቷል ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ለድንጋይና ፡ ለሕንፃ ፡ ሥራዎች ፡ የሚውሉትን ፡ ከሕጉ ፡ ውጭ ፡ አድርጓቸዋል ። የመጀመሪያው ፡ ቁ. ፪ ፡ የሕንፃ ፡ መሣሪያዎች ፡ በአፈሩ ፡ ባለቤት ፡ ሥር ፡ መሆናቸውን ፡ ሲገልጽ ፡ የሁለተኛው ፡ ቁ. ፯ ፡ ደግሞ ፡ "ድንጋዮች ፡ ከላይኛው ፡ አፈር ፡ ባለቤትነት ፡ አይለዩም ፡" ብሏል ። ዜርቮስ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷ ፡ እና ፡ ፫፻፲፫ ። በነዚሁ ፡ መሠረት ፡ በአዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ስርም ፡ ጭምር ፡ ተመሳሳይ ፡ አስተሳሰብ ፡ መደረግ ፡ አለበት ፡ ያሉ ፡ አሉ ። ቤርማን ፡ ቁ. ፫ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፶፰ ። ቢሆንም ፡ በአዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ይዞ ፡ በግልጽ ፡ ሆኖ ፡ አለመቅረቡ ፡ የሚያሳየው ፡ አስተሳሰቡ ፡ አሁን ፡ ቦታ ፡ እንደሌለው ፡ ለማሳየት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ ይቻላል ።

13. ከላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ በሚገኘው ፡ የበርማን ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ በገጽ ፡ ፩፻፴፪ ፡ የተጠቀሰ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በእንግሊዘኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተዘጋጀ ፡ የአንቀጽ ፡ ፩፻፵ ፡ ረቂቅ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ የሆነ ፡ ሀብትን ፡ ሳይጠራ ፡ ለተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ መጠበቂያ ፡ የሚሆነውን ፡ ሕግ ፡ ወስኖ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ሕግ ፡ በሚሠጠው ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጆች፡ እነዚህን ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊያውሏቸው ፡ አይችሉም ፡ ይላል ። በኋላ ፡ ግን ፡ አንዳ

ያለው ፡ ሀብት ፡” ሁሉ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነው ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ (ሀ) ፡ የአማርኛው ፡ ትርጉም ፡ ሁለተኛውን ፡ አነባበብ ፡ እንድንወስድ ፡ የሚያስገድድ ፡ ይመስላል ።

አንቀጽ ፡ ፩፻፴(ሀ) ፡ ከመንግሥት ፡ ንብረትነት ፡ ሥር ፡ የሚያስገባው ፡ "በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ያለው[ን] ፡ ሀብት፡” ብቻ ፡ ነው ፡ ካልን ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ላለው ፡ ድንጋይ ፡ ልዩ ፡ አመለካከት ፡ እንዳለ ፡ መወሰን ፡ ገና ፡ ያስፈልጋል ። በኢትዮጵያ ፡ ባህልና ፡ አሁንም ፡ በሚደረገው ፡ መሠረት ፡ የአንቀጽ ፡ ፩፻፴(ሀ) ፡ ቋንቋ ፡ ለምሳሌ ፡ ወርቅንና ፡ ፕላቲነምን ፡ የሚጠቀልል ፡ ነው ፡ ብንል ፡ አያከራክርም ፤ ጨውንና ፡ አሸዋን ፡ ይጠቀልላል ፡ ብንል ፡ ግን ፡ ድጋፍ ፡ የሚያስገኝ ፡ አይሆንም ።[14] ስለዚህ ፡ ጥያቄው ፡ በጥንቃቄ ፡ መመርመር ፡ ይኖርበታል ።

<u>የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ሀብት ፡ አመዳደብ ፤</u>

አንድ ፡ ጠቃሚ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ አስተሳሰብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ የሆነ ፡ በግልና ፡ በመንግሥት ፡ የንብረት ፡ ባለሀብትነት ፡ አከፋፈል ፡ እቅድ ፡ ውስጥ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ን ፡ መሠረታዊ ፡ አንቀጽ ፡ አድርጐ ፡ ማየት፡ ነው ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ መሬት ፡ የሚመደበው ፡ በግል ፡ ንብረቶች ፡ ውስጥ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ ለብዙ ፡ ትውልድ ፡ መሬትን ፡ በግል ፡ ጥቅም ፡ ባዋለው ፡ በእርሻ ፡ በተመሠረተው ፡ ኤኮኖሚ ፡ ለውጥ ፡ ለማምጣት ፡ ከዚህ ፡ የጠነከረ ፡ አነጋገር ፡ ያስፈልጋል ። እርግጥ ፡ ነው ፡ መንግሥት ፡ በመሬቶች ፡ ላይ ፡ መብቶች ፡ ሊኖሩት ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ መብቶቹ ፡ የተመሠረቱት ፡ እንደ ፡ ባለግል ፡ ንብረቶች ፡ ባሉ ፡ ሁኔታዎች ፡ ላይ ፡ ነው።[15] መሬት ፡ ለሕይወት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ እህልን ፡ የሚያበቅል፡ አፈር ፡ የያዘ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ (ሀ) ፡ ለእህል ፡ ምግብ ፡ ያልሆነውንና ፡ ዋጋ ፡ ያለውን ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ የሚገኙትን ፡ ሀብቶች ፡ የመንግሥት ፡ ንብረቶች ፡ ያደርጋቸዋል ።[16] አንቀጽ ፡ ፩፻፴(መ) ፡ በዚህ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ሥር ፡ ሕጋዊ፡

---

ንድ ፡ የንብረት ፡ ዓይነቶችን ፡ በመነጠል ፡ ከመንግሥት ፡ ሀብትነት ፡ ሥር ፡ ለማድረግ ፡ በማሰብ ፡ ይመስላል ፡ ይህ ፡ ረቂቅ ፡ ቀርቶ ፡ በምትኩ ፡ የአሁኑ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ ፡ ንዑስ ፡ አንቀጾች ፡ (ለ) ፡ እና ፡ (መ)፡ ተጨምረዋል ። በቀድሞው ፡ ረቂቅ ፡ የሚገኙት ፡ በጥበቃ ፡ የሚጠቀሙት ፡ ቃላት ፡ በንዑስ ፡ አንቀጾች፡ (ለ) ፡ እና ፡ (ሐ) ፡ የሚገኙት፡በመንግሥት ፡ ንብረትነት ፡ሥር ፡ ባልሆኑት ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ ላይ ፡ ቁጥጥር ፡ እንዲኖር ፡ ይመስላል ። ይህም ፡ ከሆነ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ (ሀ) ፡ ሁሉንም ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ እንደሚያደርግ ፡ አስመስሎ ፡ ማንበብ ፡ እንደማይገባ ፡ ግልጽ ፡ ይመስላል ።

14. በኢትዮጵያ ፡ የግል ፡ ሰዎች ፡ ለሚያደርጉት ፡ የጨው ፡ አወጣጥ ፡ የሚከተለውን ፡ ጠቃሚ ፡ ጽሑፍ ፡ ይመለከቷል ፡- ሃይለ ፡ ሚካኤል ፡ ምሥግና ፡ "ሶልት ፡ ማይኒንግ ፡ ኢን ፡ እንደርታ ፡” <u>ጆርናል ፡ ኦቭ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ስተዲስ</u> ፡ ፪ኛ ፡ ቮል ፡ ፪ኛ ፡ ቁጥር ፡ (፩ሺ፱፻፷፬) ፡ ገጽ ፡ ፩፻፷፯ ።

15. የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ሺ፬፻፵፬ ፡ የሚለው ፡ የመንግሥት ፡ የሆኑ ፡ ንብረቶች ፡ በልዩ ፡ ሕግ ፡ የሚተዳደሩት ፡ በተከታዮቹ ፡ አንቀጾች ፡ እንደሚብራራው ፡ "ለጠቅላላ ፡ አገልግሎት ፡ ጥቅም ፡” ሲመደቡ ፡ ነው ። የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፲፱ (ለ) ፡ የሚጠቅሰው ፡ የዘውድ ፡ ርስትና ፡ ንብረት ፡ የተባለው ፡ የተለየ ፡ የንብረት ፡ ክፍል ፡ የሚመስለው ፡ አንቀጽ፡፲፱(ለ)ን ፡ የማይተላለፍ ፡ ነው ፡ ይለዋል ።

16. ሰው ፡ ሊይዝና ፡ ሊጠቀምበት ፡ የሚችለው ፡ ክፍል ፡ ለራሱ ፡ ኑሮ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ብዙ ፡ ዝቅ ፡ ሳይል ፡ ከላይ ፡ የሚገኘው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህን ፡ አሳብ ፡ የያዘ ፡ የሚመስል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፪፻፮ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡- "የመሬት ፡ ሀብትነት ፡ (የመሬት ፡ ርስትነት)፡ ማለት ፡ <u>መሬቱን ፡ ሥራ ፡ ለማስያዝ ፡ ጠቃሚ ፡ እስከሆነው ፡ ጥልቀት</u> ፡ ያለውን ፡ የውስጥ ፡ ሀብትነትን፡ ጭምር ፡ የያዘ ፡ ነው ። ”(አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ።)
ሆኖም ፡ አንዳንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የመሬት ፡ ንብረትንነት ፡ ከመሬቱ ፡ ስር ፡ የሚገኘውን ፡ ድንጋይ ፡ እንደሚጨምር ፡ አድርገው ፡ ቁጥር ፡ ፲፪፻፮ን ፡ ተርጉመውታል ። ለምሳሌ ፡ ከላይ ፡ በግርጌ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ፡ በገጽ ፡ ፬፻፵፯ ፡ የተጠቀሰውን ፡ <u>ጣፋ ፡ ሰኝ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፤ የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥ</u>

ባለቤት ፣ ባለመኖሩ ፣ ምክንያት ፣ የተገኘ ፣ መሬት ፣ የተለቀቁ ፣ ርስቶችና ፣ ንብረቶች ፣ ጫካዎችና ፣ የአየር ፣ የባሕር ፣ ክልሎች ፣ የመሳሰሉ ፣ ንብረቶችን ፣ ይጨምራል ።[17]

ይህን ፣ አስተሳሰብ ፣ ከተቀበልን ፣ ማለት ፣ መሬቱን ፣ ለእህልና ፣ ለከብት ፣ እን ዲጠቀምበት ፣ ለግል ፣ ባለንብረት ፣ ሲሰጠው ፣ ከመሬት ፣ በታች ፣ ያለውን ፣ ለ መንግሥት ፣ ንብረትነት ፣ ይሰጣል ፣ ከመሬት ፣ በታች ፣ የሚገኘውን ፣ ድንጋይ ፣ ከመሬት ፣ በታች ፣ ከሚገኙት ፣ እንደ ፣ ወርቅ ፣ ከመሳሰሉት ፣ ከሌሎች ፣ "ውድ ፣" ማዕድኖች ፣ የተለየ ፣ አድርጐ ፣ ለመመልከት ፣ ምን ፣ ምክንያት ፣ አለ? "ውድነት፣" ስለሌለውና ፣ በጣም ፣ በብዛት ፣ ስለሚገኝ ፣ የተቀበረ ፣ የመንግሥት ፣ ገንዘብ ፣ አይደ ለምና ፣ ልዩ ፣ አስተያየት ፣ መስጠት ፣ አለበት ፣ ማለት ፣ ነውን ? ወይስ ፣ ድንጋይም ፣ እንደ ፣ አፈር ፣ ከገበሬው ፣ የዕለት ፣ ተግባር ፣ ጋር ፣ በጣም ፣ የተያያዘ ፣ በመሆኑ ፣ እንደ፣ አንድ ፣ የግል ፣ ንብረት ፣ መቆጠር ፣ ይገባዋል ?

እነዚህን ፣ ጥያቄዎች ፣ የአስተሳሰብን ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ በሚያሟላ ፣ መንገድ ፣ እና ፣ ለኢትዮጵያ ፣ አስፈላጊ ፣ ከሆኑት ፣ ነገሮች ፣ ጋራ ፣ በሚስማማ ፣ ሁኔታ ፣ ለመ መለስ ፣ መሞከር ፣ ቀላል ፣ ነገር ፣ አይደለም ። በመሬቱ ፣ ላይ ፣ ለሚኖሩት ፣ ሰዎች ፣ ድንጋይ ፣ በየቀኑ ፣ ያስፈልጋቸዋል ፤ ገበሬዎች ፣ በድንጋዩ ፣ ግንቦችንና ፣ በአንዳንድ ፣ በታዎችም ፣ ቤቶችን ፣ ለመሥራት ፣ ይችላሉ ፣ ይሰሩበታልም ። ወርቅንም ፣ ለሚስቶ ቻቸው ፣ ጉትቻ ፣ ጌጣ ፣ ጌጥ ፣ ለመሥራት ፣ ሊጠቀሙበት ፣ በቻሉ ፣ ነበር ። ምንም ፣ ድንጋይ ፣ ከወርቅ ፣ ይበልጥ ፣ በቀላሉ ፣ የሚገኝ ፣ ቢሆንም ፣ አንድ ፣ መጠነኛ ፣ የሆነ ፣ የድንጋይ ፣ መፍለጫን ፣ ለማካሄድ ፣ የተራው ፣ ገበሬ ፣ አቅም ፣ በማይፈቅድለት ፣ መሣ ሪያዎችና ፣ የማመላለሻ ፣ ዘዴዎች ፣ መጠቀም ፣ ያስፈልግ ፣ ይሆናል ።

ለዚህ ፣ ጥያቄ ፣ ሁለት ፣ የተለያዩ ፣ መልሶች ፣ ብንሰጠው ፣ ሁለቱም ፣ መልሶች፣ የሚያስከትሉትን ፣ የኤኮኖሚ ፣ ውጤት ፣ በማየት ፣ አንዱን ፣ መልስ ፣ ለመምረጥ ፣ አ

---

ልጣን ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ መልስ ፣ ሰጭ ፣ ጉዳዩን ፣ ይመለከቷል ። የሚያሳዝነው ፣ ግን ፣ እነዚህ ፣ ፍር ዶች ፣ የተሻሻለው ፣ ሕገ ፣ መንግሥት ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፴ ፣ አግባብነትን ፣ ሳይመለከቱ ፣ በመቅረታቸው ፣ ነው ። ሕገ ፣ መንግሥቱ ፣ በመሬት ፣ ውስጥ ፣ የሚገኘውን ፣ ወርቅ ፣ የመንግሥት ፣ ንብረት ፣ ሲያደርግ ፣ ቁጥር ፣ ፩ሺ.፪፻፱ ፣ ይህን ፣ ንብረትነት ፣ ሊለውጠው ፣ እንደማይችል ፣ ሁሉ ፣ በሕገ ፣ መንግሥቱ ፣ አማካ ኝነት ፣ በመሬት ፣ ውስጥ ፣ ያለው ፣ ድንጋይ ፣ የመንግሥት ፣ ንብረት ፣ ስለሆነ ፣ ቁጥር ፣ ፩ሺ.፪፻፱ ፣ ይህ ንን ፣ ንብረትነት ፣ ሊለውጥ ፣ አይችልም ። "የበላይ ፣ ሕግ ፣" አሳብን ፣ የያዘውን ፣ የተሻሻለው ፣ ሕገ፣ መንግሥት ፣ አንቀጽ ፣ ፩ሺ.፪፻፳፫ ፣ ይመለከቷል ። ቁጥር ፣ ፩ሺ.፪፻፱ ፣ በመሬት ፣ ውስጥ ፣ ስላለ ፣ ድንጋይ ፣ ስለማያወሳ ፣ ፓርላሜንቱ ፣ የሕገ ፣ መንግሥቱን ፣ አንቀጽ ፣ ልዩ ፣ ትርጉም ፣ እንደሰጠውም ፣ ለማስረ ዳት ፣ ቁጥር ፣ ፩ሺ.፪፻፱ ን ፣ ልንጠቀምበት ፣ እንችልም ። እንደ ፣ ስዊሱ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ቁጥር ፣ ፯፻፳፯ ፣ ቁጥር ፣ ፩ሺ.፪፻፺፱ም ፣ የመሬት ፣ ባለቤትነት ፣ ዝቅታው ፣ ወሰን ፣ የለውም ፣ የሚለውን ፣ የጥንቱን ፣ አስተሳሰብ ፣ ለመወሰን ፣ የተጻፈ ፣ እንጂ ፣ ከመሬት ፣ በታች ፣ ስላሉት ፣ ሀብቶች ፣ አንድ ፣ ባንድ ፣ ለማውሳት ፣ አይደለም ። ፒ ፣ ቱር ፣ ለ ፣ ኮድ ፣ ሲቪል ፣ ስዊስ ፣ (፪ኛ ፣ የፈረንሳይኛ ፣ እትም ፣ ፩ሺ.፱፻፷፪) ፣ (የደሸኖ ፣ ትርጉም) ፣ ገጽ ፣ ፬፻፺፪ ።

17. አንቀጽ ፣ ፩፻፴ (ሀ) ፣ ከመሬት ፣ በታች ፣ ላለው ፣ ድንጋይ ፣ ይበልጥ ፣ ቀጥተኛ ፣ አግባብ ፣ ያለው ፣ መስሎ ፣ ስለሚታይ ፣ በጣም ፣ አስቸጋሪ ፣ የሆኑ ፣ የትርጉም ፣ ችግሮች ፣ ያለውን ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፴ (መ) ን ፣ በዚህ ፣ ጽሑፍ ፣ ውስጥ ፣ አላብራራነውም ። የአንቀጽ ፣ ፩፻፴ (ሀ) ን ፣ መሠረተ ፣ አሳብ ፣ ሳያስ ፈልግ ፣ የሚደግም ፣ የሚመስለውን ፣ "የአፈር ፣ -----ሀብቶች ፣" የሚለውን ፣ ሐረግ ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻፴ (መ) ፣ ብናገኝም ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ ያለውን ፣ አስተያየት ፣ መርጠናል ። በተጨማሪም ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፴ (መ) ፣ "የጫካ ፤ የግጦሽ ፣ መሬት[ን] ፣" የመንግሥት ፣ ንብረቶች ፣ ቢያደርግም ፣ በኢትዮጵያ ፣ የግል ፣ ጫካዎች ፣ መኖራቸው ፣ በይፋ ፣ ታውቋል ። የ፲፱፻፶፯ ፣ ዓ. ም. የግለኛ ፣ ደን ፣ አጠባበቅ ፣ አዋጅ ፣ ቁጥ ር ፣ ፪፻፳፯ ፣ ነጋሪት ፣ ጋዜጣ ፣ ፳፬ኛ ፣ ዓመት ፣ ቁጥር ፣ ፲፯ ፣ ይመለከቷል ። በአማርኛውና ፣ በእንግሊ ዘኛው ፣ የአንቀጽ ፣ ፩፻፴(መ) ፣ ትርጉሞች ፣ ብዙ ፣ ልዩነቶች ፣ አሉ ፤ በተለይም ፣ እንግሊዘኛው ፣ "የሆነ፣ ሰው ፣ ወይም ፣ በሕግ ፣ የሰውነት ፣ መብት ፣ የተሰጠው ፣" ለሚለው ፣ አማርኛው ፣ "በተፈጥሮ ፣ ኢትዮ ጵያዊ ፣ በሆነ ፣ በማንኛውም ፣ ሰው ፣ ወይም ፣ በሕግ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ዜግነት ፣ ባለው ፣" ይላል ።

ሁንም ፡ አዳጋች ፡ ነው ። ጠቃሚ ፡ ከሆኑት ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ ብልጫ ፡ ላለው ፡ ለአውራ ፡ ጐዳና ፡ ሥራና ፡ ጥበቃ ፡ ድንጋይ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። አንቀጽ ፡ ፩፻፴ (ሀ) ፡ ድንጋይን ፡ ከመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ውጭ ፡ ያደርገዋል ፡ ብሎ ፡ መወሰን ፡ የግል ፡ ባለንብረቶች ፡ ለምንም ፡ ዓይነት ፡ የኤኮኖሚ ፡ ጥቅም ፡ ሊያውሉት ፡ ለማይችሉት ፡ ድንጋይ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ እና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መሠረት ፡ ባብዛኛው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛቶች ፡ ግምትን ፡ ምክፈል ፡ ያስገድዳሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ተቃራኒውን ፡ መልስ ፡ ከሰጠን ፡ ለመንግሥት ፡ እቅዶች ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆኑ ፡ የቀሩትን ፡ ድንጋዮች ፡ የመሬቱ ፡ ባለቤት ፡ ቢጠቀምበት፡ ወንጀልን ፡ ፈጽመሃል ፡ በማለት ፡ ክስ ፡ ሊቀርብበት ፡ ሲችል ።[18] በተጨማሪም ፡ መንግሥትም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብበት ፡ ይችላል ።[19] ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ኢንዱስትሪም ፡ ከዚህ ፡ የተነሳ ፡ ሊቃወስ ፡ ሲችል ፡ በተጨማሪም ፡ የኤኮኖሚው ፡ የግል ፡ ክፍል ፡ እንቅፋት ፡ ያጋጥመዋል ። ለግል ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ድንጋይ ፡ መንግሥት ፡ በሌሎች ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ በሚገኙት ፡ ሀብቶች ፡ በኩል ፡ አሁን ፡ እንደሚያደርገው ፡ ሁሉ ፡ ኮንሴሲዮን ፡ በመሰሉ ፡ ስምምነቶች ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ ተግባር ፡ አዳጋች ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ ችግሮች ፡ ቢገጥሙንም ፡ ሚዛናዊ ፡ ሆኖ ፡ የአስተሳሰብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ የተከተለና ፡ የአንቀጽ ፡ ፩፻፴ (ሀ) ን ፡ ግዴታዎችን ፡ የማይቃረን ፡ መፍትሔ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ክፍሎች ፡ ማቅረብ ፡ እንችላለን ። ለመጀመር ፡ ያህል ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ (ሀ) ፡ ድንጋይን ፡ እንደሌላው ፡ "በመሬቱ ፡ ውስጥ ፡" ያሉ ፡ ወይም ፡ "መሬት ፡ ያልሆኑ ፡" ሀብቶች ፡ ሁሉ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ያደርገዋል ፡ እንበል ።[20] ለዚህም ፡ አተረጓጐም ፡ የአንቀጹ ፡ ቃላት ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ አያደርጉም ። የሕጉ ፡ ቃል ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ ስለቆየው ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ስላለ ፡ ሀብት ፡ ለሚናገረው ፡ መሠረተ ፡ አሳብ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አብሮት ፡ ለሚገለጸው ፡ ለግል ፡ ሥራ ፡ የሚያደርገውን ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ በመተው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ደረጃ ፡ ይሰጠዋል ። ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ (ሀ) ፡ የግል ፡ ባለንብረቶች ፡ ለዕለት ፡ ኑሯቸው ፡ ሊይዟቸው ፡ በሚችሉት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መብቶችና ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ በሚገኘው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መብቶች ፡ መካከል ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ልዩነት ፡ የሚያደርግ ፡ ስለሚመስል ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። በብዙ ፡ መንገድ፡ ሲታይ ፡ ድንጋይ ፡ "ውድም ፡" ሆነ ፡ አልሆነ ፡ ለኤኮኖሚ ፡ ተግባሮች ፡ ሰውን ፡ ከሚማርኩ ፡ እና ፡ ጭቅጭቅ ፡ ከሚያስነሱ ፡ ማዕድኖች ፡ ይበልጥ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ "የተፈጥሮ ፡" ሀብት ፡ ነው ።

ይህንን ፡ መሪ ፡ አሳብ ፡ ከተቀበልን ፡ ለእድገት ፡ ፍላጐቶች ፡ ሲባል ፡ አንዳንድ ፡ ለውጦች ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ይሆናል ። መንግሥትም ፡ ድንጋይ ፡ የመንግ

---

18. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፶ ፡ ፯፻፵፯ ፡ እና ፡ ፯፻፴ን ፡ ይመለከቷል ።
19. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፪፻፪ ።
20. በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ በተጠቀሰው ፡ በበርማን ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ገጾች ፡ ፫፻፳፯-፫፻፴፪ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፴ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረቶች ፡ ናቸው ፡ በተባሉት ፡ ነገሮች ፡ የግል ፡ ባለቤትነት ፡ ወይም፡ "በተግባር ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ ከባለሀብትነት ፡ እኩል ፡ የሆኑትን ፡ የተወሰኑ ፡ የባለቤትነት ፡ መብቶች ፡" ሊኖሩ ፡ ይችላሉ ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ ቀርቧል ። እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መወሰን ፡ ግን ፡ የመንግሥት ፡ ንብረቶች ፡ የሚያደርገውን ፡ የአንቀጽ ፡ ፩፻፴ ፡ ክፍሎችን ፡ ከጥቅም ፡ ውጭ ፡ ያደርጋቸዋል ። "የመንግሥት ፡ ንብረት ፡" የሚለው ፡ አሳብ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጣው ፡ ከፈረንሣይ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ለሚለው፡ ለበርማን ፡ አስተያየት ፡ ምንም ፡ ድጋፍ ፡ የለውም ፤ እንዲያውም ... የዚህ ፡ አሳብ ፡ ስር ፡ የሚገኘው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ በብዙ ፡ ዓመታት ፡ በመንግሥት ፡ ባለቤትነት ፡ ለነበሩት ፡ ንብረቶች ፡ መጠሪያ ፡ ሲጠቀሙበት የነበረ ፡ ይመስላል ።

ሥት ፡ ንብረት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ለመንግሥት ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆኑት ፡ እቅዶች፡ ለሚወሰደው ፡ ድንጋይ ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ ነገሮች ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ብቻ ፡ ግምት ፡ እከፍላለሁ ፡ ሊል ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ቢሆን ፡ ለግል ፡ የእድገት ፡ እቅድ ፡ ለመሥራት ፡ ለሚፈልጉት ፡ ሰዎች ፡ በቀላሉ ፡ ለመጠቀም ፡ እንዲችሉ ፡ መደረግ ፡ አለበት። ይህን ፡ ለማድረግ ፡ የመሬቱን ፡ ባለንብረቶች ፡ ከመሬታቸው ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኘው ፡ ድንጋይ ፡ "ሕጋዊ ፡ ባለ ፡ ኮንሲሲዮን ፡" የሚያደርግ ፡ ሕግ ፡ በማውጣት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። እነዚህ ፡ የግል ፡ ባለንብረቶች ፡ በመሬታቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ድንጋይ ፡ በንግድ ፡ መልክ ፡ ሲጠቀሙበት ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ መንግሥት ፡ ያላንዳች ፡ ግምት ፡ እንዲወስድባቸው ፡ ቢደረግ ፡ ተገቢ ፡ ይመስላል ። በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ድንጋይ፡ ለመጠቀም ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ባይሆን ፡ አጠቃቀሙ ፡ በንግድ ፡ መልክ ፡ ወይም ፡ ከተፈቀደው ፡ ወሰን ፡ ያለፈ ፡ እንደሆነ ፡ ለመንግሥት ፡ የተለየ ፡ ግብር ፡ እንዲከፍሉ ፡ የሚያደርግ ፡ አንቀጽ ፡ መጨመር ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ንብረት ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ባለቤት ፡ መሆኑን ፡ ሊያስገነዝብ ፡ ይችላል ።[21]

## መደምደሚያ ፡

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴(ሀ) ፡ በብዙ ፡ ቦታዎች ፡ ላይ ፡ አተረጓጎምን ፡ የሚጠይቁ ፡ ስለ ፡ ተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ የመንግሥት ፡ ንብረትነትና ፡ ቁጥጥር ፡ የሚሆኑ ፡ አዳዲስ ፡ መሠረተ ፡ አሳቦችን ፡ አስገኝቷል ። ይህም ፡ ንዑስ ፡ አንቀጽ፡ ሁሉንም ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ ሳይሆን ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ ብቻ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ማድረጉ ፡ ግልጽ ፡ ሲመስል ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ለመሰሉ ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙ ፡ ሀብቶች ፡ ግን ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ያደረገ ፡ አይመስልም ። ከዚህም ፡ አባባል ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ጉልቶ ፡ ሊታይ ፡ የሚችለው ፡ ውጤት ፡ ከግል ፡ መሬት ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ድንጋይ ፡ የሚወስዱትን ፡ እንደ ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ የመሳሰሉ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ለድንጋዩ ፡ ግምት ፡ ከመክፈል ፡ ያድናቸዋል ። መጀመሪያውኑ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነው ፡ ስላልን ፡ "ስለ ፡ ንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡" የሚነሳ ፡ ነገር ፡ የለም ። ሆኖም ፡ ለኤኮኖሚው ፡ የግል ፡ ክፍል ፡ እድገት ፡ እንቅፋት ፡ እንዳይሆን ፡ በማሰብ ፡ ለመንግሥት ፡ እቅዶች ፡ አስፈላጊ ፡ ባልሆነው ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ድንጋይ ፡ የግል ፡ ሰዎች ፡ እንዲሰሩበት ፡ ሁኔታውን ፡ መንግሥት ፡ ማቃለል ፡ አለበት ።

21. ከመሬት ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ የመንግሥት ፡ ሀብቶችን ፡ የግል ፡ ሰዎች፡ እንዲጠቀሙበት ፡ መስጠት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው ። በ ዓ. ም. በዳግማዊ ፡ ምኒልክና ፡ በጂ ፡ ደብሊው ፡ ሌይን ፡ መካከል ፡ በተደረገው ፡ የኮንሲስዮን ፡ ስምምነት ፡ ኤርትራ ፡ በኢጣሊያ ፡ ስር፡ በነበረችበት ፡ ጊዜ ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ የነበሩት ፡ ለማንብ ፡ ሥራ ፡ የሚጠቅሙት ፡ ነገሮች ፡ የመንግሥት ፡ ንብረቶች ፡ የነበሩ ፡ ከመምሰላቸው ፡ ሌላ ፡ በኮንሴስዮን ፡ እየተሰጡ ፡ ሰው ፡ ለንግድ ፡ ይጠቀምባቸው ፡ ነበር ። ለኤርትራ ፡ ትኘ ፡ ግዛት ፡ "ኦርዲናሜንቶ ፡ ፎንዲያሪዮ ፡ ኤ ፡ ሬጎላሜንቶ ፡ ፐር ፡ ላ ፡ ሱዋ ፡ አፐሊካዚዮኔ ፡" ተብሎ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. (እ. ኤ. አ.) በቡሌቲኖ ፡ ኡፊቻሌ ፡ ቁጥር ፡ ፺፫ ፡ (ተጨማሪ) ፡ የወጣውን ፡ በተለይም ፡ የሕጉን ፡ አንቀጽ ፡ ፵፭ ፡ ይመለከቷል ። የሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ፱ ፡ ያገሬው ፡ የመሬት ፡ መብት ፡ የሚጠበቀው ፡ "[ከ] ጥንታዊው ፡ ያገሩ ፡ ልማዶች ፡ ጋራ ፡" ያልተቃረነ ፡ ከሆነ ፡ ነው ፡ ይላል ።